# የወል የሥራ ክርክር ጉዳዮችን በሰበር የማየትና የመወሰን ስልጣን የፌደራል ወይስ የክልል?  የፍርድ ትችት

*ተገኘ ዘርጋው*[*]


## *አህጽሮተ ጥናት*

የወል የአሰሪና ሰራተኛ ክርክር የፌደራል ፍርድ ቤቶች በተለይም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስልጣን ሲሆን የክልል ፍርድ ቤቶች እንደዚህ አይነት ጉዳዮችን በተመለከተ ያላቸዉ የዉክልና ስልጣን ብቻ ነዉ፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎ በተለያዩ ዉሳኔዎቹ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ ስልጣኑ ተመልክቶ የመጨረሻ ዉሳኔ የሰጠበትን የወል የስራ ክርክር በክልል ሰበር ሰሚ ችሎቶች እስካልታዩ ድረስ የፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎቱ የማየት ስልጣን እንደሌለዉ ወስኗል፡፡ ከዚህ የፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ በኂላ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዉክልና ስልጣኑ በይግባኝ ተመልክቶ ዉሳኔ የሰጠበትን ማንኛዉንም የወል የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ታይቶ ዉሳኔ እስካልተሰጠበት ድረስ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ለመታየት ብቁ አይደለም የሚለዉ ሃሳብ ሰፊ ተቀባይነት ያለዉ መርሕ ሆኗል፡፡ በመሆኑም የዚህ የፍርድ ትችት ዓላማ ይህ የፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎቱ አቋም ከሕገ መንግስቱና ከሌሎች አግባብነት ካላቸዉ ህጎች ጋር አብሮ የሚሄድ ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉን መመርመር ነዉ፡፡ ይህንን ዓላማ ለማሳካት የፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎቱ በጉዳዩ ላይ ዉሳኔ የሰጠባቸዉን ሁለት ዉሳኔዎች እና ሌሎች አግባብነት ያላቸዉን የአገሪቱን ሕጎች በጥልቀት ተመርምረዋል፡፡ የዚህ ጥናት ግኝት እንደሚያሳየዉ የፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት ሁለት ዉሳኔዎች ከኢፌዴሪ ሕገ መንግስት እና ሌሎች አግባብነት ካላቸዉ የአገሪቱ ሕጎች ጋር አብሮ የማይሄድ መሆኑ ነዉ፡፡ የወል የስራ ክርክሮች በፌደራል ፍርድ ቤቶች ብቸኛ ስልጣን ስር የሚወድቅ ሲሆን ክልሎች ይህንን አይነት ጉዳይ መመልከት የሚችሉት በዉክልና ስልጣናቸዉ ብቻ ነዉ፡፡ በሕገ መንግስቱ በተቀመጠዉ የፍርድ ቤቶች የስልጣን ዉክልና አወቃቀር መሰረት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የፌደራል ጉዳዮችን በሰበር የማየት ስልጣን የላቸዉም፡፡ ስለሆነም የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በዉክልና ስልጣናቸዉ የወል አሰሪና ሰራተኛ ጉዳይን ተመልክተዉ የመጨረሻ ዉሳኔ ከሰጡ በኂላ ይሕንን ጉዳይ በሰበር የማየት ብቸኛ ስልጣን ያለዉ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ብቻ ነዉ፡፡


***ቁልፍ ቃላት፡-*** የወል የሥራ ክርክር፣ በይግባኝ የማየት ስልጣን፣በሰበር የማየት ስልጣን፣ የውክልና ስልጣን፣ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት፣የክልል ጠቅላይ ፍርድቤት፡፡

## 1. የክልል እና የፌደራል ፍርድቤቶች አወቃቀር እና የዳኝነት ስልጣን ክፍፍል

በሕገ-መንግስቱ በግልጽ እንደተደነገገው የፌደራል መንግስቱ የራሱ ጠቅላይ፣ ከፍተኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት የሚኖረው ሲሆን ክልሎችም በተመሳሳይ ሁኔታ የራሳቸው ጠቅላይ፣ ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት እንደሚኖራቸው ተደርጓል፡፡[1] የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት የፌደራል መንግስቱ ከፍተኛ የዳኝነት አካል ሲሆን ከስረ-ነገርና ከይግባኝ ስልጣኑ በተጨማሪ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትን ማናቸውንም የመጨረሻ ውሳኔ በሰበር የማየት ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡[2] የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት በሕገ-መንግስቱ የተቋቋመ ሲሆን የፌደራል ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን በተመለከተ ግን

---

[*] LL.B degree in Law (Jimma University), LL.M degree in Business and Corporate law (Bahir Dar University), Lecturer at Bahir Dar University school of law  Email: tegegne.zergaw@gmail.com

[1] የኢፌዲሪ ሕገመንግስት ፌደራል አዋጅ ቁጥር1/1987 ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር1 በ1987 ዓ.ም፣ አንቀጽ 78 እና አንቀጽ 80

[2] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 80(1) እ 80(3)(ሀ)

የህዝብ ተወካች ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በሀገሪቱ በሙሉ ወይም በከፊል እዲያደራጅ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡[3] ሆኖም ግን ምክር ቤቱ በመላ ሀገሪቱ የከፍተኛ ፍርድቤትና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት እስከሚያቋቁም ድረስ ግን የእነዚህ ፍርድቤቶች ስልጣን በሕገ-መንግስቱ ለክልሎች በውክልና ተሰጥቷል፡፡[4] ምንም አንኳን መጀመሪያ ላይ የፌደራል ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤቶች በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች ብቻ ተቋቁመው የነበሩ ቢሆንም ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ በአምስት ክልሎች የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤቶች እንዲቋቋሙ ተደርጓል፡፡[5] በመሆኑም የፌደራል ፍርድቤቶች ባልተቋቋሙባቸው ክልሎች የክልል ጠቅላይና የክልል ከፍተኛ ፍርድቤት እንደየቅደምተከተላቸው ለራሳቸው ከተሰጣቸው መደበኛ ስልጣን በተጨማሪ በውክልና የፌደራል ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት ስልጣን እንዲመለከቱ ተደርጓል፡፡[6] ከዚህ አንፃር የክልል ጠቅላይ ፍርድቤት በውክልና የሚያየውን የፌደራል ጉዳይ አስመልክቶ የሚሰጠው ውሳኔ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት በይግባኝ የማየት ስልጣን ያለው ሲሆን የክልል ከፍተኛ ፍርድቤት በውክል አይቶ ውሳኔ በሚሰጥበት የፌደራል ጉዳይ ላይ ደግሞ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድቤት በይግባኝ እንዲመለከተው ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡[7] የክልሎችን የፍርድቤቶች አወቃቀር በምንመለከትበት ጊዜ ደግሞ የክልል ጠቅላይ፣ ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት አንደሚቋቋም በሕግ መንግስቱ በግልጽ የተደነገገ ሲሆን[8] የክልል ሕገ መንግስቶችም እነዚህን ሶስት ፍርድቤቶች አቋቁመዋል፡፡[9] የክልል ጠቅላይ ፍርድቤት በክልሉ ጉዳይ ላይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ስልጣን ያለው ሲሆን በውክልና ካገኘው፣ ስረ ነገር ከስረ ነገርና ከይግባኝ ስልጣኑ በተጨማሪ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትን በክልል ጉዳዮች ላይ የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ በሰበር የማየት ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡[10] ክልሎች የፍርድ ቤቶችን አደረጃጀትና ዝርዝር ስልጣን የሚደነግጉ ህጎችን በማውጣት የፍርድ ቤቶቹን የስረ ነገር፣ የይግባኝና የሰበር ስልጣን በዝርዝር ደንግገዋል፡፡[11] የፌደራል ፍርድ ቤቶችን በተመለከተ የፌደራል ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 25/1988 የፌደራል ፍርድ ቤቶችን ስልጣን የደነገገ ሲሆን የፍርድ ቤቶቹን የስረ ነገር፣ የይግባኝ እና የሰበር ስልጣንን በዝርዝር አስቀምጧል፡፡ በዚህ አዋጅ መሰረት የፌደራል ፍርድቤቶች በጠቅላላው ሕገ-መንግስቱን፣ የፌደራል መንግስቱን ሕጎች፣ አለም አቀፍ ስምምነቶችን መሰረት በማድረግ የሚነሱ ጉዳዮችን፤ በሕገ-መንግስቱ የፌደራል ተብለው ከተገለፁ ቦታዎች የሚመነጩ ጉዳዮችን እና በፌደራል መንግስቱ ሕግ ተገልፀው በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ የዳኝነት ስልጣን እንዳላቸው ተደንግጓል፡፡[12]

---

[3] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 78(2)

[4] ዝኒ ከማሁ፣ 78(2) እና 80(2፣4፣5)

[5] የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት ማደራጃ አዋጅ ቁጥር 322/1995፣ *ነጋሪት ጋዜጣ፣* (1995)፣ በአንቀጽ 2 መሰረት በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ በደቡብ፣ በጋምቤላ፣በአፋር እና በሶማሌ ክልሎች የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት ተቋቁሟል

[6] የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት በግርጌ ማስታወሻ 2 እንደተገለፀው፣ አንቀጽ 78(2) እና 80(2፣4፣5)

[7] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 80(5-6)

[8] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 78(3)

[9] የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ መንግስት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር 59/1994፣ *ዝክረ ሕግ፣* (1994) ፣ አንቀጽ 46ና 47፤ እና የተሻሻለው የ1994 ዓ.ም የኦሮሚያ ክልል ሕገ መንግስት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር 46/1994 አንቀጽ 64

[10] የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት በግርጌ ማስታወሻ 2 እንደተገለፀው፣ አንቀጽ 80(2) እ 80(3)(ለ)

[11] የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድቤቶችን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 11/1988 (እንደተሻሻለው)

[12] የፌደራል ፍርድቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988፣ *ነጋሪት ጋዜጣ* (1988) 13፣ 1988 አንቀጽ 3 እና ከአንቀጽ 4-15

ከዚህ አንፃር የዚህ ጥናት አላማ ለፌደራል ፍርድቤቶች የተሰጠውን አጠቃላይ የዳኝነት ስልጣንን ማብራራት እና መተንተን ባለመሆኑ ጥናቱ ትኩረቱን የሚያደርገው ትንሽ ግራ በሚያጋባውና አከራካሪ በሆነው ከፌደራል ሕጎች የሚመነጩ ጉዳዮች የመመልከት ስልጣን የማን ነው? በሚለው ጉዳይ ላይ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ሁለት አቋሞች የሚንፀባረቁ ሲሆን የመጀመሪያው አቋም ከፌደራል ሕጎች የሚመነጩ ማለትም በሕገ መንግስቱ በአንቀጽ 55 መሰረት የህዝብ ተወካዮች እንዲያወጣቸው ተለይተው ከተሰጡ ሕጎች የሚመነጩ ወይም እነዚህን ሕጎች መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች የፌደራል ፍርድቤቶች ብቸኛ ስልጣን ናቸው የሚል ነው፡፡[13] እንደዚህ አቋም አራማጆች አባባል ከፌደራል ሕግ የሚመነጩ ወይም ይህንኑ መሰረት ያደረጉ የትኛዎቹም ጉዳዮች የፌደራል ጉዳዮች በመሆኑናቸው ለፌደራል ፍርድቤቶች የተሰጡ ብቸኛ ስልጣኖች ሲሆኑ ከዚህ ውጭ ያሉት ጉዳዮች በሙሉ የክልሎች ስልጣን ይሆናሉ ማለት ነው፡፡ በመሆኑም የወንጀል ሕግ፣ የአሠሪና ሠራተኛ ሕግና የንግድ ሕግ የፌደራል ሕጎች በመሆናቸው እነዚህን ሕጎች መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች የፌደራል ጉዳዮች በመሆኑቸው እነዚህን በተመለከተ የክልል ፍርድቤቶች የውክልና ስልጣን ካልሆነ በስተቀር ጉዳዮቹን በብቸኝነት የማየትም ሆነ የጣምራ ስልጣን የላቸውም፡፡[14] ሁለተኛው አቋም ደግሞ ምንም እንኳን የፌደራል ፍርድቤቶች ማደረጃ አዋጅ የፌደራል ሕጎችን መሰረት አድርገው የሚነሱ ጉዳዮች የፌደራል ጉዳዮች ናቸው ቢልም የፌደራል ጠቅላይ፣ ከፍተኛንና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤቶች የፍትሐብሔርና የወንጀል የስረነገርና የይግባኝ ስልጣንን በሚዘረዝርበት ጊዜ የፌደራል ሕጎችን መሰረት አድርገው የሚነሱ ሁሉንም ጉዳዮች በዝርዝሩ ውስጥ ያላካተተ ሲሆን ከፌደራል ሕጎች ውስጥ የተወሰኑ ጉዳዮችን ብቻ መርጦ ነው በዝርዝሩ ያካተተው፡፡[15] በመሆኑም አዋጁ ከፌደራል ሕጎች ከሚመነጩ ጉዳዮች መካከል የተወሰኑ ጉዳዮችን ብቻ ለይቶ ለፌደራል ፍርድቤቶች የሰጠ በመሆኑ የፌደራል ፍርድቤቶች ስልጣን በአዋጁ በግልጽ ተለይተው በተሰጡት በእነዚህ ጉዳዮች ብቻ የተወሰነ እንጅ በሁሉም ከፌደራል ሕግ በሚመነጩ ጉዳዮች ላይ አይደለም በማለት ይከራከራሉ፡፡ በመሆኑም አዋጁ ከፌደራል ሕጎች የሚመነጩ ሁሉንም ጉዳዮች ለፌደራል ፍርድቤቶች በሙሉ ዘርዝሮ ባለመስጠቱ ለፌደራል ፍርድቤቶች ተለይተው ባልተሰጡ ሆኖም ግን ከፌደራል ሕግ በሚመነጩ ጉዳዮች የክልል ፍርድቤቶች ጉዳዩን የማየት ስልጣን ያላቸው መሆኑን ይናገራሉ፡፡[16]

ሆኖም ግን ይህንን አቋም በሚያራምዱ ሰዎች መካከል ሁለት የተለያዩ አመለካከቶች የሚንፀባረቁ ሲሆን የመጀመሪያው አመለካከት በአዋጅ ቁጥር 25/1988 በዝርዝር ለፌደራል ፍርድቤቶችየተሰጡ ጉዳዮች ለፌደራል ፍርድቤቶች በብቸኝነት የተሰጡ ስልጣኖች በመሆናቸው በአዋጁ በግልጽ ተዘርዝረው ለፌደራል ፍርድቤቶች ባልተሰጡ ሆኖም ግን የፌደራል ሕጎችን መሰረት አድርገው በሚነሱ ጉዳዮች ላይ የክልል ፍርድቤቶችብቸኛ ስልጣን አላቸው የሚል ነው፡፡[17] ሁለተኛው አመለካከት ደግሞ በፌደራል ፍርድቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ በግልጽ ተለይተው እና ተዘርዝረው ለፌደራል ፍርድቤቶች ባልተሰጡ ጉዳዮች የክልል

---

[13] Abebe Mulatu, The Court System and Questions of Jurisdiction under the FDRE Constitution and Proclamation 25/26 "in Proceedings of the Symposium on the Role of Courts in the Enforcement of the Constitution*, Vol. I, 2000,* P.129-130

[14] የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 2 እንደተገለፀው፣ አንቀጽ 55(3-5)

[15] የፌደራል ፍርደ ቤቶች አዋጅ በግርጌ ማስታዎሻ ቁጥር 13 እንደተገለፀው ፣ አንቀጽ 4-15

[16] Asefa Feseha, Federalism Teahing Material, Justice and legal system research Institute, 2009, p.460,available at https://ethiopianlaw.weebly.com/uploads/5/5/7/6/5576668/federalism.pdfLast accessed on 16-02-2019)

[17] አበበ ሙላቱ በግርጌ ማስታዎሻ ቁጥር 14 እንደተገለፀው ፣ ገጽ 130

ፍርድቤቶች ያላቸው ስልጣን የራሳቸው ብቸኛ ስልጣን ሳይሆን የጣምራ ስልጣን ነው የሚል ነው፡፡ ለዚህም የሚቀርበው ምክንያት የመጀሪያውን አመለካከት ብንከተል የፌደራል ፍርድቤቶች ከፌደራል ሕጎች በሚመነጩ ጉዳዮች ምንም አይነት ስልጣን እንዳይኖራቸው የሚያደርግ ሲሆን ይህ ደግሞ የፌደራል ፍርድቤቶችን ተፈጥሯዊ ስልጣን ሙሉ በሙሉ እንደመንጠቅ ይቆጠራል፡፡ በመሆኑም የፌደራል ፍርድቤቶች የራሳቸውን ተፈጥሮአዊ ጉዳዮች እንዳይመለከቱ ማደረግ ፈጽሞ የማይታሰብ በመሆኑ እነዚህን ጉዳዮች የክልል ፍርድቤቶችም ሆነ የፌደራል ፍርድቤቶች ጉዳዩ የሚነሳበትን ቦታ መሰረት አድርገው በጣምራነት የመመልከት ስልጣን አላቸው በማለት ይከራከራሉ፡፡[18] እነዚህን ሁለት አቋሞች በምንመረምርበት ጊዜ የሁለተኛው አቋም የተሻለ ይመስላል፡፡ ምክንያቱም እነዚህን ጉዳዮች የማየት ስልጣን የክልል ፍርድቤቶች ብቸኛ ስልጣን ከሆነ በፌደራል ሕጎች ላይ የፌደራል ፍርድቤቱ ምንም አይነት ሚና እንዳይኖራቸው ያደርጋል፡፡ በመሆኑ አንድ ከፌደራል ሕግ የሚመነጭ ጉዳይ[19] ለፌደራል ፍርድቤቶች በብቸኝነት እስካልተሰጠ ድረስ የፌደራል መንግስቱ በሚያስተዳድራቸው አካባቢዎች የፌደራል ፍርድቤቶች እንዲሁም በክልል በሚነሱ ጉዳዮች የክልል ፍርድቤቶች ጉዳዩን የመመልከት ስልጣን አላቸው፡፡

## 2. ለክልሎች በጣምራነትና በውክልና የተሰጠ የፌደራል ጉዳይን በሰበር የማየት ስልጣን

የክልል ጠቅላይ ፍርድቤቶች በውክልና የሚያዩትን የፌደራል ጉዳይ በይግባኝ የማየት ስልጣን የፌደራል ፍርድቤቶች ስልጣን እንደሆነ በሕገ-መንግስቱ በግልጽ ተቀምጧል፡፡[20] ይህንንም መነሻ በማድረግ የክልል ፍርድቤቶች በውክልና የተመለከቱትን የፌደራል ጉዳይ በሰበር የማየት ስልጣን የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ነው የሚል አቋም መያዝ ተገቢነት አለው፡፡ ሆኖም ግን አከራካሪው እና ሕጋዊ ትንታኔ የሚጠይቀው ጉዳይ የክልል ፍርድቤቶች በጣምራ ስልጣን የሚመለከቷቸውን የፌደራል ጉዳዮች በይግባኝና በሰበር የማየት ስልጣን የማን ነው? የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት በፌደራል ጉዳዮች ላይ ከፍተኛና የመጨረሻ የዳኝነት ስልጣን ያለው አካል በመሆኑ ክልሎች በውክልና የሚያዩትን የፌደራል ጉዳይ ብቻ ሳይሆን በጣምራ ስልጣንነት በስረነገር የሚመለከቷቸውንም የፌደራል ጉዳዮች በይግባኝ የማየት ስልጣን አለው ብለው የሚከራከሩ ሰዎች አሉ፡፡ ይህንን አቋም የሚደግፉ ሰዎች እንደሚሉት ለክልል በጣምራነት በተሰጡ የፌደራል ጉዳዮች ላይ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ጉዳዮችን በይግባኝም ሆነ በሰበር የመመልከት ስልጣን እንዳለው ከሕገ መንግስቱ እና ከፍርድቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ የጣምራ ንባብ መረዳት እንደሚቻል ይጠቁማሉ፡፡[21] ሁለተኛው አቋምና ይህ አጥኚ የሚደግፈው አቋም ደግሞ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት በሰበር የማየት እንጅ በይግባኝ የማየት ስልጣን ሊኖረው አይገባም የሚል ነው፡፡ ምክንያቱም የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 80ና የፌደራል ፍርድ ቤቶችን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/88 በምንመለከትበት ጊዜ የፌደራል ፍርድቤቶች የይግባኝ ስልጣን የክልል ፍርድቤቶች በውክልና በሚያዩት የፌደራል ጉዳይ ላይ የተገደበ እንጅ የክልል ፍርድቤቶች በጣምራ ስልጣን በስረ ነገር ደረጃ የሚመለከቱትን የፌደራል ጉዳይ እንደሚጨምር የሚያመላክት ነገር የለም፡፡ አንዳንድ የህግ

---

[18] አሰፋ ፍስሃ (ዶ/ር) በግርጌ ማስታዎሻ ቁጥር 17 እንደተገለጸው፣ ገጽ 461

[19] የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት በግርጌ ማስታወሻ 2 እንደተገለፀው፣ አንቀጽ 55(3))

[20] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 80(6)

[21] Sileshi Zeyohannes, Constitutional Law II, Teaching material, Prepared under the sponsorship of Justice and Legal System Research Institut,2009, p. 203

ምሁራን እንደሚሉት የፌደራል ሕጎች ተጠቅሰው የሚመሰረቱ ክሶች ምንም እንኳን ጉዳዮቹ የፌደራል ጉዳዮች ቢሆኑም በተግባር ጉዳዮቹ በክልል ፍርድቤቶች በስረ ነገርና በይግባኝ መታየታቸው የማይነቀፍ መሆኑን አምነው እነዚህን ጉዳዮች ግን የክልል ሰበር ሰሚ ችሎቱ በሰበር መመልከቱ የሚነቀፍና ተግቢ ያልሆነ ተግባር እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡[22]

ሁለተኛው መሰረታዊ ጉዳይ ደግሞ ክልሎች በጣምራነት በሚያዩዋቸው የፌደራል ሕጎችን መሰረት አድርገው የሚቀርቡ ጉዳዮችን በሰበር የማየት ስልጣን የማን ነው? የሚለው ነው፡፡ በዚህ ጥያቄ ላይ ሁለት አመለካከቶች ያሉ ሲሆን የመጀመሪያው አመለካከት የፌደራል ሕጎች መሰረት ተደርገው በሚመሰረቱ የትኞቹም ክሶች ጉዳዩ ከክልል ፍርድ ቤትም ይነሳ ከፌደራል ፍርድቤት ጉዳዩን በሰበር የማየት ስልጣን ያለው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ነው የሚል ነው፡፡ መሃሪ ረዳኢ(ዶ/ር) እንደሚሉት ከፌደራል ሕጎች በሚመነጩ ጉዳዮች ላይ የሚቀርብን ክስ ወደክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ማቅረብ በፌደራል ሕግ ላይ የመጨረሻና አስገዳጅ ትርጉም መስጠት ያለበት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ነው የሚለውን የሕገ መንግስቱን ግልጽ ድንጋጌ የሚጋፋ ነው፡፡ በመሆኑም የፌደራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት እነዚህን የመሳሰሉ ጉዳዮችን የማስተናገድ መብትም ሆነ ሃላፊነት ያለው ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የፌደራል ሕግ መሰረት ተደርጎ የተወሰኑ ጉዳዮችን በሰበር ማስተናገድ የለበትም፡፡ ስለዚህ የአሠሪና ሠራተኛና መሰል የፌደራል ሕጎች መሰረት ተደርጎ በክልል ፍርድቤቶች ውሳኔ የተሰጠባቸው ጉዳዮች ላይ ጥቅም ላይ የዋለው ሕግ የፌደራል ሕግ ስለሆነ ይህ ሕግ በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋሉን ማረጋገጥና መተርጎም የፌደራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን በመሆኑ የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት እነዚህን የመሳሰሉ ጉዳዮች ሊያስተናግዱ አይገባም በማለት ይከራከራሉ፡፡ በመሆኑም በፌደራል ሕግ የሚዳኙ ጉዳዮችን የክልል ሰበር ሰሚ ችሎቶች እንዳያዩ በማድረግ በዚህ ረገድ የሚከሰተው የሰበር ሰበር ሊቀር የሚገባው ሲሆን[23] እነዚህን ጉዳዮች የክልል ፍርድቤቶች በሰበር ማየታቸው ተቀባይነት የለውም የሚል አመለካከት አላቸው፡፡[24] በአጠቃላይ ማንኛውም የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ የፌደራል ሕግ ከሆነው የአሠሪና ሠራተኛ ሕግ የሚመነጭ በመሆኑ ጉዳዩ ለክልል ፍርድቤቶች የተሰጠው በጣምራነት ይሁን በውክልና ይህንን ጉዳይ የክልል ተዋረዱን ጠብቆ ከመጣ በኋላ በሰበር የማየት ብቸኛ ስልጣን ያለው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ነው፡፡ ከዚህ በተቃራኒ ያለው አመለካከት ደግሞ የፌደራል ፍርድቤቶች በይግባኝም ሆነ በሰበር የማየት ስልጣን ለክልል ፍርድቤቶች በውክልና በተሰጠ ጉዳይ ላይ የተገደበ በመሆኑ ከፌደራል ሕጎች የሚመነጩ ሆነው ለክልሎች በጣምራነት በተሰጡ ጉዳዮች የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ጉዳዩን በይግባኝም ሆነ በሰበር የማየት ስልጣን የለውም የሚል ነው፡፡[25] ይህ አጥኚ የመጀመሪያው አቋም የተሻለ ነው የሚል እምነት አለው፡፡ ምክንያቱም በሕገ መንግስቱ ለክልል ፍርድቤቶች በውክልና የተሰጠን የፌደራል ጉዳይ በይግባኝ የማየትና

---

[22] *መሃሪ ረዳኢ*፣ የሰበር ሰበርና ተግዳሮቶቹ በኢትዮጵያ፣ *ሚዛን ሎው ሪቪው* ፣ ቅጽ 9 ቁጥር 1፣ 2007 ዓ.ም፣ ገጽ 193 Avilable at https://www.ajol.info/index.php/mlr/article/view/124829/114342 Accsesd on 4/12/2017

[23] *ዝኒ ከማሁ*፣ ገጽ 193

[24] *ዝኒ ከማሁ*፣ ገጽ 194

[25] Abdisa Dashura, Implication of Cassation Over Cassation In The Ethiopian Federal Context: With Special Reference To the Principle of Self-Determination, a Thesis Submitted to Addis Ababa University, College of Law and Governance, unpublished, 2014 p.97 avilable at http://etd.aau.edu.et/bitstream/handle/1234567 accsessed on 1/3/2019

ማንኛውንም የመጨረሻ ፍርድ በሰበር የማረም ስልጣን የተሰጠው ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት በመሆኑ ነው፡፡[26]

## 3. የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይን በስረ ነገር፣ በይግባኝና በሰበር የማየት ስልጣን

### ሀ. የስረ ነገር እና የይግባኝ ስልጣን

ስለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 377/2003[27] በምንመለከትበት ጊዜ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይን የወልና የግለሰብ የስራ ክርክር በማለት የከፈላቸው ሲሆን ጉዳዩ የግል የስራ ክርክር ከሆነ መደበኛ ፍ/ቤቶች እንዲሁም ጉዳዩ የወል የስራ ክርክር ከሆነ ደግሞ የአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርዶች እንዲመለከቷቸው ስልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡[28] በዚህም መሰረት የክልል ወረዳ ፍርድቤቶች በጥቅሉ የግል የስራ ክርክሮችን እንዲመለከቱ ስልጣን የተሰጣቸው ሲሆን የደሞዝና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን፣ ስንብትንና የዲሲፕሊን እርምጃዎችን፣ የስራ ውል መቋረጥ/መሰረዝን፣ የስራ ሰዓትን፣ የተከፋይ ሂሳብን፣ ፈቃድንና ዕረፍትን፣ የቅጥርና የስንብት ማስረጃ ሰርተፍኬት መስጠትንና የጉዳት ካሳን የሚመለከቱ ክሶችን የመዳኘት ስልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡[29] ከአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በሚቀርቡ ጉዳዮች ላይ የክልል ከፍተኛ ፍርድቤት የይግባኝ ስልጣን ብቻ ያለው ሲሆን የወረዳ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ የስራ ክርክር ስልጣንን፣ የማህበር ምዝገባ(ስረዛን) በተመለከተ ሚንስቴሩ የሚሰጠውን ውሳኔ፣ የስራ ሁኔታ ተቆጣጣሪ የሚሰጠውን ትዕዛዝ፣ እና በአንቀጽ 20(3) መሰረት መብትና ግዴታዎችን ለጊዜው ማገድን ተከትሎ ሚንስቴሩ (በክልል ደረጃ ደግሞ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ) የሚሰጠውን ውሳኔ በመቃወም የሚቀርቡ ይግባኞችን የማየት ስልጣን አለው፡፡[30] ከዚህ ላይ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳዮችን በውክልና ሳይሆን በጣምራ ስልጣንነት ለክልል ፍርድቤቶች መሰጠቱን በጽኑ የሚቃወሙ ሰዎች መኖራቸው መታወቅ ያለበት ሲሆን ሕጉ ግን በዚህ መልኩ የክልል ፍርድቤቶች በግለሰብ የስራ ክርክር ላይ የስረ ነገርና የይግባኝ ስልጣን እንዳላቸው በግልጽ አስቀምጧል፡፡[31] አዋጁ የወል የስራ ክርክሮችን በተመለከተ እነዚህን ጉዳዮች የመዳኘት ስልጣን ከክልል መደበኛ ፍርድቤቶች ይልቅ ለጊዚያዊና ቋሚ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የሰጠ ሲሆን የቦርዶቹን ስልጣን በዝርዝር አስቀምጧል፡፡[32] ከዚህ ላይ መረሳት

---

[26] የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት በግርጌ ማስታወሻ 2 እንደተገለፀው ፣ አንቀጽ 80(3)(ለ) እና አንቀጽ 80(5)

[27] ይህ አዋጅ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ አዋጅ ቁጥር ቁጥር 1156/2011 የተተካ ሲሆን ይህ አዋጅም ቢሆን የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይን የወልና የግል የስራ ክርክር በማለት በመክፈል የወል የስራ ክርክሮችን በአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድና የግል የስራ ክርክርን ደግሞ በመደበኛ ፍርድቤቶችእንዲታዩ አድርጓል

[28] የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 10ኛ ዓመት ቁጥር 12፣ 1996፣ አንቀጽ 138 እና 142

[29] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 139

[30] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 139(2)

[31] ሕሩይ ውቤ እንደሚለው የክልል ፍርድቤቶች ሁሉንም የፌደራል ጉዳዮች ያለምንም ገደብ የማየት ስልጣን ያልተሰጣቸው በመሆኑ የፌደራል ፍርድ ቤት ስልጣን የሆኑትን ጉዳዮች የሚያዩበት ስልጣን የሚመነጨው በሕገ መንግስቱ በተሰጣቸው የውክልና ስልጣን ብቻ ነው፡፡ በዚህ ውክልና መሰረት በክልሎች የሚነሱ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳዮችን በትክክለኛው መንገድ በውክልና መመልከት የሚችሉት የክልል ጠቅላይ ፍርድቤትና ከፍተኛ ፍርድቤቶች ብቻ ናቸው ፡፡ በመሆኑም የክልል የወረዳ ፍርድቤቶች ከፌደራል ሕግ የሚመነጩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳዮችን ለመዳኘት የሚያስችል ሕገ መንግስታዊ መሰረት የላቸውም፡፡ ይሁን እንጅ አዋጁ ከዚህ በተለዩ ሁኔታ ክርክሮች ከክልል የወረዳ ፍርድ ቤቶች ጀምሮ በቀጥታ እንዲታዩ አድርጓል፡፡ Hiruy Wubie, The Settlement of Individual and Collective Labour Disputes under Ethiopian Labour Law, *E-Journal of International and Comparative Labour Studies*, Volume 2, No. 1, 2013, p.21

[32] በዚህም መሰረት የጊዜያዊ የአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ የአየር መንገድ አገልግሎት፣ የኤሌክትሪክ/መብራት ሀይል አገልግሎት፣ የውሃና የከተማ ጽዳት አገልግሎት፣ የከተማ አውቶብስ አገልግሎት፣ ሆስፒታሎች፣ ክሊኒኮች፣ የመድሀኒት ማከፋፈያ ድርጅቶችና የመድሀኒት መሸጫ ቤቶች፣ የእሳት አደጋ አገልግሎትና የቴሌ ኮሙኒኬሽን

የሌለበት ነገር ቢኖር በቋሚም ይሁን በጊዜያዊ ቦርዱ በክርክር ሂደት የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ሁሉ የመጨረሻ በመሆናቸው በይግባኝ ችሎቱ ክርክር አይነሳባቸውም፡፡[33] የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድቤት በቦርድ በተሰጠ ውሳኔ ላይ የህግ ነጥብን መሰረት አድርጎ የሚቀርብ ይግባኝን የማየት ስልጣን በብቸኝነት የተሰጠው ሲሆን በዚህ አግባብ በይግባኝ የሚሰጥ ውሳኔም የመጨረሻ እንደሆነ በግልጽ ተመልክቷል፡፡[34]

## ለ. የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይን በሰበር የማየት ስልጣን

ከዚህ በላይ በዝርዝር እንደቀረበው የአሠሪና ሰራተኛ ጉዳይን በሰበር የማየት ስልጣንን በተመለከተ ሁለት አቋሞች ያሉ ሲሆን፣ የመጀመሪያው አቋም የአሠሪና ሠራተኛ ሕግን ጨምሮ ማንኛውንም የፌደራል ሕግ መሰረት አድርገው የሚመሰረቱ ክሶች ምንም እንኳን ጉዳዩ በክልል ፍርድቤቶች ታይቶ የመጣ ቢሆንም ጉዳዩን በሰበር አይቶ የመወሰን ስልጣን የክልል ፍርድቤቶች ሳይሆን የፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት ነው የሚል ነው፡፡ ይህንን አቋም የሚያራምዱ ሰዎች እንደሚሉት ከሕገ መንግስቱ አኳያ ሲታይ የፌደራል ሕግ በሆነው የአሠሪና ሠራተኛ ሕግ ላይ የመጨረሻና አስገዳጅ ትርጉም መስጠት ያለበት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት በመሆኑ ምንም እንኳን ጉዳዮ በስረ ነገር ደረጃ በክልሎች ታይቶ የመጣ ቢሆንም የፌደራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የፌደራል ሕጎች ተጠቅሰው የሚመሰረቱ ጉዳዮችን የማስተናገድ መብትም ሆነ ሃላፊነት አለው፡፡ እንደእነዚህ ሰዎች አባባል ሰበር በባህርይው በሕጉ ላይ የመጨረሻ ትርጉም የመስጠት ሃላፊነት እንደመሆኑና የክልል ፍርድ ቤቶችም የፌደራል ሕግን መሰረት ያደረገ ጉዳዩን በሰበር ተመልክተው ውሳኔ መስጠት የማይቻላቸው በመሆኑ እነዚህን ጉዳዮችን የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር የማስተናገድ ምንም አይነት ህጋዊ ስልጣን የለውም፡፡ በመሆኑም የአሠሪና ሠራተኛና መሰል የፌደራል ሕጎች መሰረት ተደርጎ በክልል ፍርድቤቶች ውሳኔ የተሰጠባቸው ጉዳዮች ቢኖሩ ጥቅም ላይ የዋለው ሕግ የፌደራል ሕግ እስከሆነ ድረስ ይህ ሕግ በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋሉንና መተርጎሙን ማረጋገጥ ያለበት የፌደራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመሆኑ የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት እነዚህን የመሳሰሉ ጉዳዮች ሊመለከቱ አይገባም በማለት ያስረዳሉ፡፡[35] አሰፋ ፍስሃ(ዶ/ር) ይህንን ተመሳሳይ አቋም የሚደግፍ ሲሆን እንዲያውም ለክልሎች በጣምራነት በተሰጡ የፌደራል ጉዳዮች የፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት በተግባር እንደሚያደርገው ጉዳዩን በሰበር የማየት ስልጣን ብቻ ሳይሆን ያለው ጉዳዩን በይግባኝ የማየት ስልጣን አለው በማለት ይከራከራል፡፡[36] በሁለተኛ ደረጃ የሚንፀባረቀው አቋም ደግሞ ምንም እንኳን ጉዳዮቹ ከፌደራል ሕግ የሚመነጩ ቢሆኑም በአዋጅ ቁጥር 25/1988 ወይም በሌላ አግባብነት ባለው ሕግ ለፌደራል ፍርድቤቶችተለይተው ባልተሰጡ ጉዳዮች የክልል ፍርድቤቶች የጣምራነት ስልጣን ያላቸው

---

አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶችን በተመለከተ የሚነሱ የደመወዝና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን የማየት ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ ቋሚ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳዮች ወሳኝ ቦርድ በበኩሉ ጉዳዮች በቅድሚያ በአስማሚው አካል ታይተው ካልተፈቱ በአንቀጽ 136 የተመለከቱትን (ህዝባዊ አገልግሎት የሚሰጡ) ድርጅቶች ጨምሮ አዲስ የስራ ሁኔታዎችን መመስረት፣ የህብረት ስምምነትን የተመለከቱ አለመግባባቶች፣ የሠራተኞች አቀጣጠርና ዕድገት አሰጣጥ፣ አጠቃላይ የሰራተኞችንና የድርጅቱን ህልውና የሚነኩ ጉዳዮች፤ ዕድገትን፣ ዝውውርንና ስልጠናን በተመለከተ አሰሪው የሚወስዳቸውን ዕርምጃዎች፣ የሰራተኞችን ቅነሳ እንዲሁም በአንቀጽ 160 ላይ የተመለከቱትን ህገ-ወጥ ተግባራት በተመለከተ የሚቀርቡ ጉዳዮችን የማየት የስረ-ነገር ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡በግርጌ ማስታዎሻ ቁጥር 28 እንደተገለጸው፣ አንቀጽ 136፣ 142(3)፣ 147(2)፤ እና የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 466/1997 ዓ.ም *ፌደራል ነጋሪት ጋዜ*ጣ( 1997) ዓ.ም፣ አንቀጽ 2(1) እና (2))

[33] የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ አዋጅ ቁጥር ቁጥር 1156/2011፣*የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ* (2011)፣ አንቀጽ 142(1)፣ አንቀጽ 147(1) እና አንቀጽ 153

[34] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 140(1) እና አንቀጽ 154 እና አንቀጽ 140(2)

[35] መሐሪ ረዳኢ በግርጌ ማስተዎሻ ቁጥር 23 እንደተገለፀው ፣ገጽ 193

[36] አሰፋ ፍስሃ (ዶ/ር) በግርጌ ማስታዎሻ ቁጥር 17 እንደተገለጸው ፣ ገጽ 463-464

በመሆኑ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት በሰበር ስልጣኑ ማየት የሚችለው ለክልል ፍርድቤቶች በውክልና የተሰጡ ጉዳዮችን እንጅ በጣምራነት የሚያዩዋቸውን የፌደራል ጉዳዮች አይደለም በማለት ይከራከራሉ፡፡ ከዚህ አንፃር ለክልል ፍርድቤቶች በውክልና በተሰጡ ጉዳዮች የክልል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር የማየት ስልጣን የሌለው ሲሆን በጣምራነት በተሰጠው የፌደራል ጉዳዮች ግን ጉዳዩን በሰበር የመመልከት ስልጣን አለው በማለት ይከራከራሉ፡፡[37]

ሁለቱን አቋሞች በምንመለከትበት ጊዜ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት በሰበር ስልጣኑ ማየት የሚችለው ለክልል ፍርድቤቶች በውክልና የተሰጡ የፌደራል ጉዳዮችን እንጅ በጣምራነት የሚስተናገዷቸውን የፌደራል ጉዳዮች አይደለም የሚለው አቋም የተሻለ ተቀባይነት አለው፡፡ ሆኖም ግን ለክልሎች በጣምራነት በተሰጡ የፌደራል ጉዳዮች የመጨረሻ የሰበር ውሳኔ የሚሰጠው የክልል ጠቅላይ ፍርድቤት ብቻ እንደሆነ አድርጎ መቁጠሩ ግን ሕገ መንግስቱን ያገናዘበ አይደለም፡፡ ለክልል ፍርድቤቶች በጣምራነት የተሰጡ የፌደራል ጉዳዮች ወደክልሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መቅረብ የሚኖርባቸው ቢሆንም በዚህ የሰበር ችሎት የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ሳይሆን የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን በሰበር የማየት ስልጣን አለው፡፡ ምክንያቱም በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80(3)(ሀ) መሰረት የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ማንኛውንም የመጨረሻ ውሳኔን ተመልክቶ በሰበር የማረም ስልጣን ያለው በመሆኑ ነው፡፡ የፌደራል ሕጎች በሀገሪቱ ወጥ የሆነ አተረጓጎምና አፈፃፀም እንዲኖራቸው የማድረግ ሃላፊነት የተጣለበት በፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ላይ በመሆኑ ጉዳዮቹ በክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ታይተው ክልል ላይ ይቋጩ ከተባለ ጠቅላይ ፍርድቤቱ ይህንን ሚናውን በተገቢው ሁኔታ መወጣት እንዳይችል ያደርገዋል፡፡ በመሆኑም የአሠሪና ሠራተኛ ሕጉ አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመፍጠር ከሚያስችሉ ህጎች መካከል አንዱና ዋነኛው በመሆኑ ይህንን ህግ በተመለከተ በሀገሪቱ ወጥ የሆነ አተረጓጎምና አፈፃፀም እንዲኖር ለማድረግ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እነዚህን ጉዳዮች በሰበር የግዴታ መመልከት ይኖርበታል፤ የመመልከት ስልጣንም ተሰጥቶታል፡፡

ወደአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ በምንመጣበት ጊዜ እንደዚህ አጥኝ እምነት በአዋጁ በግልጽ ለክልል የወረዳ፣ የከፍተኛና ጠቅላይ ፍርድቤቶች በጣምራነት በተሰጡ የፌደራል ጉዳዮችን በሰበር የማየት ስልጣን ያለው የክልል ጠቅላይ ፍርድቤት ነው፡፡ ምክንያቱም በአሠሪና ሠራተኛ አዋጁ የተወሰኑ ጉዳዮችን አይቶ የመዳኘት የስረ ነገር ስልጣን በጣምራነት ለክልል ፍርድቤቶች በግልጽ የሰጠ በመሆኑና እነዚህ ጉዳዮች ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 መሰረት ለፌደራል ፍርድቤቶች በግልጽ ተለይተው የተሰጡ ጉዳዮች ባለመሆናቸው ለክልል ፍርድቤቶች እንደተሰጡ ጉዳዮች ተደርገው መቆጠር አለባቸው፡፡ ስለዚህ ከላይ የቀረበውን የመጀመሪያውን አቋም በመደገፍ እነዚህን ጉዳዮች በክልልና በፌደራል ፍርድቤቶች የጣምራነት ስልጣን የሚወድቁ በመሆናቸው ጉዳዩን በሰበር የማየት ስልጣን ሊኖረው የሚገባው የክልል ፍርድቤት ነው፡፡ ሆኖም ግን ምንም እንኳን ጉዳዮቹ በጣምራነት ለክልል ፍርድቤቶች የተሰጡ ቢሆንም የፌደራል ሕግ ከሆነው የአሠሪና ሠራተኛ ሕግ የመነጩ ጉዳዮች በመሆናቸው የክልል ጠቅላይ ፍርድቤት በሰበር የሰጠው ውሳኔ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ መሆን የለበትም፡፡ ከዚህ አንፃር በዚህ ጉዳይ ላይ የክልል ሰበር ችሎቱ የሰጠውን የመጨረሻ ውሳኔ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት በሰበር ሊመለከተው እንደሚገባ ከሕገ መንግስቱ ንባብ በቀላሉ መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህ ላይ አሁን የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት

[37] አብዲሳ ዳሹራ በግርጌ ማስታዎሻ ቁጥር 28 እንደተጠቀሰ፣ ገጽ 97

እየተከተለው ያለው አሰራር ትክክለኛነት ያለውና ሕጉን ያገናዘበ ነው፡፡ የፌደራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 94106 ላይ በክልሉ ውስጥ የሰበር ሰሚ ችሎት ካለ በክልል ወረዳ ፍርድቤት የተጀመረ አንድ ጉዳይ በዚያው ክልል በሰበር ሳይመረመር ወደ ፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብና ሊስተናገድ አይገባውም የሚል ውሳኔ በ2006 ዓ.ም ሰጥቷል፡፡ ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይን መሰረት አድርጎ የቀረበ ሲሆን በክልሉ የወረዳ ፍርድቤት ተጀምሮ በዞን ከፍተኛ ፍርድቤት በይግባኝ ቀርቦ የስር ፍርድቤት ውሳኔ ከፀና በኋላ አመልካቹ ጉዳዩን በቀጥታ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሲያቀርብ ሰበር ሰሚ ችሎቱ መጀመሪያ ወደ ክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ሳይቀርብ ወደዚህ ችሎት መቅረብ አልነበረበትም ብሎ ክሱን ውድቅ አድርጎታል፡፡[38] ምንም እንኳን ጉዳዩ መሰረት ያደረገው ለክልሎች በጣምራነት በተሰጠ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ በመሆኑ የፍርድ ቤቱ ውሳኔ ተገቢና የሚነቀፍ ባይሆንም አንዳንድ የሕግ ምሁራን ይህንን ውሳኔ በመቃዎም በጽሁ ተችተውታል፡፡[39] እንደ አጥኝው እምነት ጉዳዩ ለክልሎች በጣምራነት የተሰጠ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ የደረሰበት ድምዳሜ የሚነቀፍ አይደለም፡፡

አሁን ለተያዘው ጉዳይ ጠቃሚ የሚሆነው ለአሰሪና ሰራተኛ ቦርዶች በስረ ነገርና ለከፍተኛ ፍርድቤት በይግባኝ በተሰጡ የወል የስራ ክርክሮች የአሠሪና ሠራተኛ አዋጁ በግልጽ የተለየ አካሄድ የተከተለ በመሆኑ እነዚህን ጉዳዮች አስመልክቶ ቦርዶች የወሰናቸውን ውሳኔዎች በሰበር የማየት ስልጣን የማን ነው የሚለውን በጥልቀት መመርመር ያስፈልጋል፡፡ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጁ ለክልል ወረዳ ፍ/ቤቶች በግል የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳዮች የስረ-ነገር ስልጣን ከሰጠና እነዚህንም ጉዳዮች የክልሉ ከፍተኛ ፍርድቤቶች በይግባኝ የሚያዩበትን አሰራር ካስቀመጠ በኃላ በልዩ ሁኔታ የወል የአሰሪና ሰራተኛ ክርክሮችን በስረ ነገርና በይግባኝ የማየት ብቸኛ ስልጣን እንደየቅደምተከተላቸው ለአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርዶችና ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት ሰጥቷል፡፡[40] በሌላ አነጋገር የአሠሪና ሠራተኛ አዋጁ የግል የስራ ክርክሮችን ከክልል የወረዳ ፍ/ቤቶች ጀምሮ በቀጥታ በክልል ፍርድቤቶች በስረነገርና በይግባኝ እንዲታዩ ያደረገ ቢሆንም ከዚህ አካሄድ በተለየ ሁኔታ በየክልሎቹ የተቋቋሙት ጊዜያዊና ቋሚ ቦርዶች የሚሰጧቸውን ውሳኔዎች በይግባኝ የማየት ስልጣን ግን ለክልል ፍርድቤቶች ሳይሆን በቀጥታ ለፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድቤት ብቻ ሰጥቷል፡፡ የተወሰኑ ጉዳዮችን ለክልል ወረዳ ፍርድቤቶች ከሰጠና ጉዳዮቹም በክልል ፍርድቤቶች በይግባኝ እንዲታዩ በግልጽ ካስቀመጠ በኃላ የቦርዱን ውሳኔዎች በይግባኝ የማየት ስልጣን ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲሆን ያደረገበት ምክንያት ይህ ጉዳይ የክልል ፍርድቤቶች ጣምራ ስልጣን እንዳይሆንና በዚህ ጉዳይ ላይ የፌደራል ፍርድቤቶች ብቸኛ ስልጣን እንዲኖራቸውና ክልሎች ጉዳዩን በውክልና ስልጣናቸው ብቻ እንዲመለከቱት በመፈለጉ ነው ብሎ መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑን ከሕገ መንግስቱ፣ ከአሠሪና ሠራተኛ አዋጁ ብሎም ከፌደራል ፍርድቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ጣምራ ንባብ መረዳት የምንችለው በአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርዶች የሚወሰኑ ጉዳዮች የፌደራል ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣኖች መሆናቸውን ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የክልል ጠቅላይ ፍርድቤቶች በቦርዶቹ የሚሰጡ ውሳኔዎችን በይግባኝ ማየት የሚችሉት በአሠሪና ሠራተኛ አዋጁ በቀጥታ በተሰጣቸው የጣምራ ስልጣን ሳይሆን በሕገ መንግስቱ በተቀመጠው የውክልና ስልጣን መሆኑን በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የክልል ፍርድቤቶች በነዚህ ጉዳዮች ላይ የተሰጣቸው በይግባኝ የማየት ስልጣን የጣምራ ስልጣን

[38] ኢትዮ-ቴሌኮም ደቡብ ምዕራብና ጋምቤላ ሪጅንና ወ/ሮ ሳባ መንገሻ፣የሰበር መዝገብ ቁጥር 94106፣ ቅጽ 16
[39] መሐሪ ረዳኢ በግርጌ ማስተዎሻ ቁጥር 23 እንደተገለፀው ፣ገጽ 187-188
[40] የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ በግርጌ ማስታዎሻ ቁጥር 28 እንደተገለጹው ፣ አንቀጽ 14

ቢሆን ኑሮ አዋጁ የተወሰኑ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳዮችን ከወረዳ ጀምሮ እስከ ክልል ጠቅላይ ፍርድቤቶች ድረስ በስረ ነገርና በይግባኝ የሚታዩበትን አግባብ ካስቀመጠ በኋላ በቦርዶቹ የሚወሰኑ ጉዳዮችን በይግባኝ የማየት ስልጣን በልዩ ሁኔታ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ብቻ አይሰጥም ነበር፡፡ በመሆኑም አዋጁ ይህንን ያደረገው በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የክልል ፍርድቤቶች የውክልና ስልጣን እንጅ የጣምራ ስልጣን እንዳይኖራቸው ለማድረግና እነዚህ ጉዳዮች የፌደራል ፍርድቤቶች ብቸኛ ስልጣን እንዲሆኑ በማሰብ ነው ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡

እነዚህ ጉዳዮች ከላይ በቀረበው አግባብ የፌደራል ጉዳዮች መሆናቸውን ካየን በቀጣይ በጥልቀት መታየት ያለበት ነገር እነዚህን ጉዳዮች በሰበር የማየት ስልጣን የፌደራል ፍርድቤት ነው ወይስ የክልል ፍርድቤቶች የሚለውን ጥያቄ ነው፡፡ ከዚህ በላይ በነበረው ገለፃ የፌደራል ፍርድቤቶች በብቸኝነት በተሰጣቸው ስልጣንና ክልሎች በሕገ መንግስቱ በተሰጣቸው ውክልና መሰረት የሚመለከቱት ማንኛውም የፌደራል ጉዳይን በይግባኝ የማየት ስልጣን የፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት እንጅ የክልል ጠቅላይ ፍርድቤቶች እንዳልሆነ ተመልክተናል፡፡ ምክንያቱም በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80(3)(ለ) መሰረት ለክልል ጠቅላይ ፍርድቤት ጉዳዮችን በሰበር የማረም ስልጣን የተሰጣቸው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ባለባቸው <u>የክልል ጉዳዮች</u> (ሰረዝ የተጨመረ) ብቻ እንደሆነ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ የአሠሪና ሠራተኛ ቦርድ የሚወስነው ማንኛውም ውሳኔ በይግባኝ የሚቀርበው ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት እንደሆነ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ አንቀጽ 140ና 154 በግልጽ ተመላክቷል፡፡ እነዚህ ጉዳዮች የፌደራል ጉዳዮች በመሆናቸው የክልል ፍርድቤቶች በውክልና የሚመለከቷቸው ሲሆን በአሰሪና ሰራተኛ ቦርዱ የሚወሰኑ የወል የስራ ክርክሮች የክልል ፍርድቤቶች በስረ ነገር ደረጃ ሳይሆን ጉዳዩን በውክልና በይግባኝ የማየት ስልጣን ብቻ እንደተሰጣቸው ግልጽ ነው፡፡ ምክንያቱም አዋጁ የግል የስራ ክርክሮች በክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት ከታዩ በኋላ ጉዳዩን በይግባኝ የማየት ስልጣን በግልጽ የክልል ይግባኝ ሰሚ ፍርድቤቶች እንደሆነ በአንቀጽ 139 ካስቀመጠ በኋላ ከዚያው አንቀጽ ቀጥሎ ባለው አንቀጽ 140 በቦርዱ የሚወሰኑ የወል አሰሪና ሰራተኛ ክርክሮችን የማየት ስልጣ የክልል ይግባኝ ሰሚ ፍርድቤት ሳይሆን በግልጽ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት ስልጣን መሆኑን ያስቀመጠ በመሆኑ ነው፡፡ አዋጁ እነዚህ ጉዳዮች በክልል የመደበኛ ይግባኝ ሰሚ ፍርድቤቶች በጣምራነት እንዲታዩ ቢፈልግ ኖሮ በአንቀጽ 139 ከተመለከተው አቋም በተለየ ሁኔታ ጉዳዮቹን በይግባኝ የማየትን ስልጣን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት አይሰጥም ነበር፤ ወይም የክልል ይግባኝ ሰሚ ችሎቶች ጉዳዩን በይግባኝ እንደሚመለከቱት በግልጽ ያስቀምጥ ነበር፡፡ ከዚህ ላይ አሁን የወጣውን አዋጅ በምንመለከትበት ጊዜ ከአሁን ቀደም የነበረው አዋጅ በአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ የሚሰጡ ውሳኔዎችን በይግባኝ የማየት ስልጣን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት እና በውክልና ደግሞ ለክልል ጠቅላይ ፍርድቤት መስጠቱ ተገቢ አለመሆኑን በመገንዘብ ጉዳዩን በፌደራልም ሆነ በክልል ደረጃ ያሉ ከፍተኛ ፍርድቤቶች በስረ ነገር ስልጣን እንዲመለከቱት አድርጓል፡፡ በመሆኑም ከአሁን በፊት ይህንን ጉዳይ የክልል ጠቅላይ ፍርድቤቶች የሚመለከቱት በሕገ መንግስቱ በተቀመጠው ውክልና መሰረት ሲሆን ከአሁን በኋላ ግን የክልል ከፍተኛ ፍርድቤቶች በቦርዱ ውሳኔ የተሰጠበትን የወል የስራ ክርክር በጣምራ ስልጣን በስረ ነገር ደረጃ በይግባኝ የማየት ስልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡[41] ከዚህ በተጨማሪ ሕገ-መንግስቱን በምናይበት ጊዜ የክልል ፍርድቤቶች በሰበር የማየት ስልጣን የተሰጣቸው በክልል ጉዳይ ላይ በተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ላይ እንጅ በግልጽ ለፌደራል

[41] አዲሱ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ አንቀጽ 155

መንግስቱ ተለይተው የተሰጡና የክልል ፍርድቤቶች በውክልና በሚመለከቷቸው የፌደራል ጉዳዮችን እንዳልሆነ በቀላሉ መረዳት ይቻላል፡፡[42] በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80(6) እንደተቀመጠው የክልል ጠቅላይ ፍርድቤት በውክልና ስልጣኑ የሚያያቸውን ጉዳዮች በይግባኝ የማየት ስልጣኑ ተሻግሮ የሚሄደው ወደ ፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድቤት በመሆኑ ይህ አይነት ጉዳይ በክልሉ ሆነ በፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድቤት የመጨረሻ ውሳኔ ሲሰጥበት ጉዳዩን በሰበር የማየት ስልጣን ሊኖረው የሚገባው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንጅ የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት አይደለም፡፡

በአጠቃላይ ምንም እንኳን የፌደራል ፍርድቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይን በግልጽ ለፌደራል ፍርድቤቶች በብቸኝነት ያልሰጠ ቢሆንም በኋላ የወጣው የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ አንዳንድ ጉዳዮችን በግልጽ ለይቶ ለክልል ፍርድቤቶች ከሰጠ በኋላ የወል የስራ ክርክሮችን ለአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርዱና ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት በመስጠት የፌደራል ፍርድቤቶች ጉዳይ እንዲሆንና በዚህ ዙሪያ ላይ የክልል መደበኛ ፍርድቤቶች ጉዳዩን በውክልና በይግባኝ የማየት ስልጣ ብቻ እንዲኖራቸው አድርጓል፡፡ ከዚህ ላይ ግልጽ ሊሆን የሚገባው ነገር አሁን በተግባር የአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ የወሰነውን ውሳኔ የክልል ጠቅላይ ፍርድቤቶች የሚመለከቱት በአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ መሰረት ሳይሆን በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80(2) በተሰጣቸው የውክልና ስልጣን ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የአሠሪና ሠራተኛ ሕጉ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ላይ ልዩ ሕግና ከፌደራል ፍርድቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ በኋላ የወጣ ሕግ በመሆኑ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይን በተመለከተ ያለውን የፍርድቤቶች የስልጣን ክፍፍል ለመወሰን የበላይነትና ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው ሕግ ነው፡፡

## የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መ/ቁ 94839 እና የሰ/መ/ቁ 99426 የውሳኔ ይዘት

በመ/ቁ 94839[43] የተመለከተው ጉዳይ በመተሃራ ስኳር ፋብሪካና በ139 ሰራተኞች መካከል በተፈጠረ የስራ ክርክር ሲሆን ክርክር የተጀመረው ሠራተኞቹ በፋብሪካው ላይ በምስራቅ ኦሮሚያ አሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ በመሰረቱት ክስ ነው፡፡ የከሳሾችም የክስ ይዘት ባጭሩ ሲታይ ከተከሳሽ ጋር መስርተው የነበረውን የስራ ውል አዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 19(7)ን በሚቃረን ሁኔታ ከስራ የተቀነሱ መሆኑን ጠቅሰው እርምጃው ሕገ ወጥ ነው ተብሎ ወደ ስራ እንዲመለሱ ወይም ሕጋዊ ክፍያዎች እንዲከፈሏቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ተከሳሽ ለክሱ በሰጠው መልስ የግል የስራ ክርክር በመሆኑ በቦርዱ ሊታይ እንደማይገባ፣ ክሱም በይርጋ የታገደ መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃዎሚያነት ያነሳ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃም ተገቢ ነው ያለውን የክርክር ነጥብ አንስቷል፡፡ ቦርዱም ጉዳዩን መርምሮ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን እንዳለው ሆኖም ግን የአብዛኛዎቹ ሰራተኞች ክስ በይርጋ የታገደ መሆኑንና የ14 ሰራተኞች ደግሞ ምንም እንኳን ክሱ ጊዜውን ጠብቆ የቀረበ ቢሆንም ጥያቄው በክፍያ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ በቦርዱ ስልጣን እንደማይወድቅና የወረዳ ፍርድቤት ስልጣን መሆኑን ጠቅሶ መዝገቡን ዘግቷል፡፡ ከሳሾቹ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ በሰጠው ውሳኔ የከሳሾች ጥያቄ ከራሳቸው አልፎ የሌሎችን ሰራተኞች የሚነካ በመሆኑ ክርክሩ የወል የስራ ክርክር እንደሚሆንና ጉዳዩም በይርጋም አልታገደም በማለት

[42] የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት በግርጌ ማስታዎሻ ቁጥር 2 እንደተገለፀው ፣ አንቀጽ 80(3)(ለ)

[43] መትሃራ ስኳር ፋብሪካና ጥበቡ እሸቱ (139 ሰዎች) የሰበር መዝገብ ቁጥር 94839፣ቅጽ 16

የቦርዱን ብይን ሽሮ ቦርዱ በፍሬ ነገር ግራ ቀኙን አከራክሮ ዳኝነት ሊሰጥበት ይገባል በማለት ጉዳዩን መልሶታል። ተከሻሹም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ጉዳዩን ወደ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት አቅርቦታል። የሰበር ሰሚ ችሎቱም ይህ ጉዳይ በክልል ደረጃ የመጨረሻ ውሳኔ ተሰጥቶበት የቀረበ ጉዳይ ነው ወይ? የሚለውን በጭብጥነት ይዞ ከመረመረ በኋላ ጉዳዩ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሳይታይ ወደ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ አይገባም በማለት አቤቱታውን ውድቅ አድርጎታል። ፍርድ ቤቱ እንደሚለው አንድ የስራ ክርክር በፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ችሎት ለመስተናገድ እንዲችል ጉዳዩን ለመወሰን ስልጣን በተሰጣቸው አካላት በተዋረድ ታይቶ የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበት መሆኑ መረጋገጥ እንደሚገባው ከኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሐ)ና ከአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10(3) ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል። የሰበር ችሎቱ እንዳተተው ክርክሩ በምስራቃዊ ኦሮሚያ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የተጀመረና በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ታይቶ የቦርዱ ውሳኔ ከመሻሩ ውጭ በኦሮሚያ ሕገ መንግስትና የክልሉ ፍርድቤቶች እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ መሰረት ጉዳዩ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ውሳኔ የተሰጠበት ባለመሆኑ ጉዳዩ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ችሎት ቀርቦ ሊታይ የማይችልበት ሌላ ህጋዊ ምክንያት የለም። በአጠቃላይ ጉዳዩ በፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት ሊስተናገድ በሚችል ደረጃ የመጨረሻ ውሳኔ ያልተሰጠበ በመሆኑና የቀረበው የስራ ክርክር የሚመራው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት በመሆኑ በክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ያልታየ ውሳኔን ችሎቱ የሚያስተናግድበት አግባብ የለም በማለት ወስኗል።[44]

ሁለተኛው የሰ/መ/ቁ 99426ን[45] በምንመለከትበት ጊዜ ደግሞ ጉዳዩ በአሽራፍ አግሪካልቸራልና ኢንዱስትሪያል ኃ/የተ/የግል ማህበርና በእነ አየለ አድማሱ 113 ሰዎች መካከል የነበረ የስራ ክርክር ሲሆን ጉዳዩ የተጀመረው በምእራብ አማራ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ነው። ከሳሾች ባቀረቡት ክስ ተከሻሽ የመዋቅር ለውጥ ባልተደረገበት ሁኔታ የመዋቅር ለውጥ በመስራት ላይ ስለሆንኩኝ የሰው ሃይል ለመቀነስ አስፈልጎኛል በማለት ሰራኞችን በሚጎዳ መልኩ የቀነሰን በመሆኑ ቅነሳው ህግ ወጥ ነው ተብሎ ያልተከፈልን ደመወዝ ተከፍሎን ወደ ስራ እንመለስ ሲሉ ጠይቀዋል። ቦርዱም አመልካች የፈጸመው የሰራተኞች ቅነሳ በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 29-50 ያሉትን ተከትሎ ያልፈፀመው ስለሆነ አስፈላጊው ክፍያ ተከፍሎ ወደ ስራ እንዲመልሳቸው ወስኗል። ተከሳሽም በውሳኔው ቅር በመሰኘት ወደ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ቅሬታውን በማቅረቡ ፍርድ ቤቱም የቦርዱን ውሳኔ አጽንቷል። ተከሳሹም በቦርዱና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድቤት የተሰጠውን ውሳኔ ለማስቀየር ጉዳዩን ለፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት አቀርቧል። የሰበር ችሎቱም ጉዳዩ ከመታየቱ በፊት ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው ነጥብ እንደዚህ አይነት የአሠሪና ሠራተኛ ክርክር በክልሉ የአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ ከተጀመረና በይግባኝ በክልል ፍርድቤት ከታየ በኋላ በክልሉ ሰበር ሰሚ ሳይታይ ወደ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መቅረብ አለበት የሚለው በጭብጥነት ይዞ ጉዳዩን መርምሯል። ችሎቱም ከአሁን ቀደም በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ በመዝገብ ቁጥር 95298፣ 98381፣ እና 94839 ትርጉም የሰጠበት መሆኑን በማስታዎስ አመልካች የክልሉ ጠቅላይ ፍርድቤት በይግባኝ የወሰነውን የመጨረሻ ውሳኔ ወደ ክልሉ ሰበር ማቅረብ ሲገባው ወደ ፌደራል ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት ማቅረቡ

44 ዝኒ ከማሁ

45 አሽራፍ አግሪካልቸራልና ኢንዱስትሪያል ኃ/የተ/የግልማህበርና አየለ አድማሱ(113 ሰዎች)፣ የሰበር መዝገብ ቁጥር 99426 (ያልታተመ)

መሰረታዊ የስነ ስርዓት ሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ጉዳዩ ከክልል ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ በፊት ለፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ የሚታይበት አግባብ እንደሌለ ወስኗል፡፡

**በሁለቱ መዝገቦች ላይ የሰበር ችሎቱ የሰጠውን ውሳኔ በተመለከተ የቀረበ ትችት**

በመጀመሪያ ደረጃ ችሎቱ ለአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርዶችና ለክልል መደበኛ ፍርድቤቶች የተሰጡ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳዮቹን አንድ አድርጎ በመቁጠር ማንኛውም ከአሠሪና ሠራተኛ አዋጁ የመነጨ ጉዳይ በተመሳሳይ ስነ ስርዓት መስተናገድ አለበት የሚል አቋም ይዞ ጉዳዮቹን መመርመሩ ተገቢ አልነበረም፡፡ በመሆኑም ችሎቱ ጉዳዩ ከክልሎች የመጣ መሆኑን እንጅ ክልሎች ይህንን ጉዳይ ያዩት በራሳቸው ብቸኛ ስልጣን የሚወድቅ በመሆኑ ነው? ወይስ ጉዳዩ የፌደራል ጉዳይ ሆኖ በጣምራነት ወይም በውክልና ያገኙት በመሆኑ ነው? የሚለውን በጭብጥነት ይዞ አልመረመረም፡፡ ከዚህ አንፃር ችሎቱ ጉዳዩን በሚመረምርበት ጊዜ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳዮች የወልና የግል ጉዳይ ተብለው እንደተከፋፈሉና እነዚህ ጉዳዮች በተለያዩ ስነ ስርዓቶች የሚስተናገዱ መሆኑን ከግምት ውስጥ አላስገባም፡፡ ከላይ በዝርዝር እንደተመለከትነው የወል የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳዮች በአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ እንደሚታዩና ቦርዱ የሰጠው ውሳኔ በይግባኝ የማየት ስልጣን በብቸኝነት የተሰጠው ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤቶች ሲሆን የክልል ፍርድቤቶች በቦርዱ የተሰጠውን ውሳኔ በይግባኝ ማየት የሚችሉት በሕገ መንግስቱ በተሰጣቸው የውክልና ስልጣን ብቻ ነው፡፡ በሕገ መንግስቱ የተሰጣቸው ስልጣን ባይኖር ኖሮ የክልል ፍርድቤቶች ይህንን ጉዳይ በይግባኝ የማየት ስልጣን አይኖራቸውም ነበር፡፡ ምክንያቱም የአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ በግል የስራ ክርክር ጉዳዮች ላይ የክልል ይግባኝ ሰሚ ፍርድቤቶች ጉዳዩን እንደሚያዩት በግልጽ ካስቀመጠ በኋላ ቦርዱ ውሳኔ የሰጠበትን የወል የስራ ክርክር በይግባኝ የማየት ስልጣን ደግሞ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት ለይቶ የሰጠ በመሆኑ ነው፡፡ ሆኖም ግን የሰበር ፍርድ ቤቱ ይህንን መሰረታዊ ጉዳይ አንድም ቦታ ላይ ሳይጠቅስ ሁሉንም የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳዮች የመመልከት ስልጣን ሙሉ በሙሉ ለክልል ፍርድቤቶች እንደተሰጠ አድርጎ በመቁጠር ጉዳዩን መርመሩና የወል የስራ ክርክሮች በክልል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሳይታዩ በቀጥታ ለፌደራል ሰበር መቅረብ አይችሉም ብሎ መወሰኑ ተቀባይነት የለውም፡፡ ሕገ መንግስቱ የክልል ጠቅላይ ፍርድቤት በውክልና የሚያያቸውን የፌደራል ጉዳዮች በይግባኝ የማየት ስልጣን የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ እንደሆነ በግልጽ ያስቀመጠ ሲሆን ሕገ መንግስቱ የክልል ፍርድቤቶች በውክልና የተመለከቷቸውን የፌደራል ጉዳዮች ወደ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ሳይቀርቡ ወደ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መቅረብ የለባቸውም የሚል አቋም ቢኖረው ኖሮ ይህንን ድንጋጌ አያስቀምጥም ነበር፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት ባልተቋቋመባቸው ክልሎች የክልል ጠቅላይ ፍርድቤት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ስልጣን በውክልና ስለሚያይ ራሱ በውክልና ያየውን ጉዳይ እንደገና በሰበር ይይ ቢባል ጉዳዩን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድቤት በይግባኝ የማቅረብ መብትን የሚጋፋ ነው፡፡ ቦርዱ በወሰነው ውሳኔ ላይ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ወይም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድቤት በይግባኝ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ነው ተብሎ በግልጽ በአዋጁ ባይቀመጥ ኖሮ የስራ ክርክር ወሳኝ ቦርድና የክልል ጠቅላይ ፍርድቤት የተለያዩ ውሳኔዎች ቢሰጡ ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድቤት የማቅረብ መብት ስለሚኖር የክልል ጠቅላይ ፍርድቤት ጉዳዩን በሰበር ይይ ቢባል ይህ የይግባኝ መብት ይቀራል ወይም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድቤት በይግባኝ ካያቸው በኋላ ለሰበር ወደ ክልል ጠቅላይ ፍርድቤት ይመለሳል ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ተቀባይነት ያለውና ህጉን የተከተለ አካሄድ አይደለም፡፡ በአጠቃላይ የሰበር ችሎቱ ከወረዳ ፍርድቤት ጀምሮ እስከ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ድረስ

ተለይተው ለክልሎች በግልጽ የተሰጡ የግል የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳዮች ለቦርዱ ከተሰጡ የወል የስራ ክርክሮች የተለዩ መሆናቸውን ቢገነዘብና የክልል ፍርድቤቶች እነዚህን ጉዳዮች በምን አግባብና ብቃት እንደሚያዩዋቸው ቢመረምር ኖሮ አሁን ከደረሰበት የተሳሳተ ድምዳሜ ላይ አይደርስም ነበር፡፡

ከዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ነገር በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 3 መሰረት የፌደራል መንግስቱ ህጎችን መሰረት አድርጎ የሚነሳ ክርክር ለፌደራል ፍርድቤቶች የተሰጠ ስልጣን በመሆኑ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ በፌደራል መንግስቱ ሕግ የማውጣት ስልጣን ስር የሚወድቅ በመሆኑ ከዚህ ህግ የሚመነጭ ማንኛውም ጉዳይ በፌደራል ፍርድቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቅ ነው፡፡ ሆኖም ግን የአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ ከወል የስራ ክርክር በስተቀር የክልል ፍርድቤቶች የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይን እንዲመለከቱ ስልጣን ሰጥቷል፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ የአሠሪና ሠራተኛ ቦርድ ባየው ጉዳይ ላይ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድቤት በውክልና በይግባኝ ተመልክቶ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ እንደሚሆን በግልጽ የተቀመጠ በመሆኑ ጉዳዩን የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት በሰበር የሚመለከተው ከመሆኑ በቀር የክልል ጠቅላይ ፍርድቤት ጉዳዩን በሰበር የማየት ሕገ መንግስታዊ ስልጣን የለውም፡፡ ከዚህ አንፃር የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ይህንን መሰረታዊ ነጥብ ሳይመረምር የደረሰበት ድምዳሜ ከአሠሪና ሠራተኛ አወጁና ከሕገ መንግሰቱ ጋር አብሮ የሚሄድ አይደለም፡፡

ሰበር ፍርድ ቤቱ በሁለቱም መዝገቦች ላይ በሰጠው ውሳኔ ላይ የሚስተዋለው ሁለተኛው ችግር ደግሞ ጉዳዩ ለጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የቀረበበትን ምክንያት የተረዳበት አግባብና ይህንን መሰረት በማድረግ የደረሰበት ድምዳሜ ጉዳዩንና ሕጉን በደንብ ያላገናዘበ መሆኑ ነው፡፡ ጉዳዩ ለፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ የቻለው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድቤት በይግባኝ ጉዳዩን የተመለከተው በሕገ መንግስቱ በተሰጠው ውክልና መሰረት በመሆኑ የሰበር አቤቱታ መቅረብ ያለበት ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ነው በሚል እምነት ነው፡፡[46] ከዚህ አንፃር የሰበር ችሎቱ በጭብጥነት ይዞ መመርመር የነበረበት የቀረበው ጉዳይ የወል ወይስ የግለሰብ የስራ ክርክር? የወል የስራ ክርክር ከሆነስ ጉዳዩን በስረ ነገር የመመልከት ስልጣን ያለው መደበኛ ፍርድቤት ወይስ የአሠሪና ሠራተኛ ቦርድ? ይህንን ጉዳይ በይግባኝ መመልከት የሚችለው የፌደራል ፍርድቤቶች ወይስ የክልል ፍርድ ቤቶች? በዚህ አግባብ የመጣን ጉዳይ በሰበር የማየት ስልጣንስ የማን ነው? ጉዳዩን ክልሎች የሚመለከቱት ከሆነስ በምን ብቃት ነው? የሚሉትን ጉዳዮች መሆን ሲገባው ይህንን አላደረገም፡፡ የሰበር ችሎቱ ጉዳዩ የወል የስራ ክርክር እንደሆነ፣ ጉዳዩን የማየት ስልጣን በስረ ነገር ደረጃ ለአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ ብሎም በይግባኝ ደረጃ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት የተሰጠ መሆኑን፣ እና ይህንን ጉዳዩ የክልሎቹ ጠቅላይ ፍርድቤቶች የተመለከቱት በውክልና መሆኑን አንድም ቦታ ላይ አላነሳም፡፡ ከትክክለኛ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ደግሞ የሰበር ችሎቱ በጭብጥነት ይዞ መፍታት የነበረበት ይህንን የጉዳዩን ዓይነትና አመጣጥ እንጅ የተከራካሪ ወገኖች ማንነት ባለመሆኑና ሁሉም የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳዮች ለክልል ፍርድቤቶች በብቸኝነት እንደተሰጡ አድርጎ በመቁጠር ጉዳዩን የመረመረ በመሆኑ ከዚህ የተሳሳተ ድምዳሜ ላይ ሊደርስ ችሏል፡፡

[46] ለአብክመ ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቀን 04/02/07 ያለፈ ሰበር ይፈቀድልኝ በሚል በአሸራፍ አግሪካልቸራልና ኢንዱስትሪያል ኃ/የተ/የግል ማህበር የቀረበ አቤቱታ(አቤቱታው የቀረበው ጉዳዩን ወደ ፌደራል ሰበር ሰሚ በመሄዱ ምክንያትና የሰበር ችሎቱም ጉዳዩ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሳይቀረብ ወደፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት መቅረብ አይችልም ብሎ ውሳኔ በመስጠቱ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የማቅረቢያ የጊዜ ገደቡ በማለፉ የሰበር አቤቱታው እንዲፈቀድለት ለመጠየቅ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡)

ከዚህ ላይ የሰበር ፍርድ ቤቱ ለትችት በቀረቡት ሁለት መዝገቦች ላይ የተመለከተውን ውሳኔ ለመስጠት ከአሁን በፊት ውሳኔ የሰጠበትን የሰበር መዝገብ ቁጥር 95298 መሰረት ማድረጉን በምናይበት ጊዜ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ይህንን ስህተት ለምን እንደሰራ በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል። ምክንያቱም በሰበር መዝገብ ቁጥር 95298 የቀረበው ጉዳይ በክልል የወረዳ ፍርድቤት ተጀምሮ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድቤት በይግባኝ የተወሰነ የግል የስራ ክርክር እንጅ በውል የስራ ክርክር ጉዳይ ባለመሆኑ በእነዚህ ሁለት መዝገቦች ከቀረበው ጉዳይ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የለውም። በመዝገብ ቁጥር 95298 ላይ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የሚከተለውን ትንታኔና ውሳኔ ሰጥቷል[47]:-

> *የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይን በተመለከተ በክልሎች ውስጥ የሚነሱ የግል የስራ ክርክር ጉዳዮችን ተቀብሎ የማየት የስረ ነገር ስልጣን የተሰጠው ለክልል የመጀመሪያ ፍርድቤት ለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 3771996 አንቀጽ 138(1) ተደንግጓል። ይህ ድንጋጌውም በአዋጅ ቁጥር 25/1988 የተደነገገውን ዓይነት የተከራካሪ አካላትን ማንነት ከግንዛቤ ውስጥ ካለማስገባቱም ሌላ ድንጋጌው የተካተተበት አዋጅ ቁጥር 377/1996 የወጣው ከአዋጅ ቁጥር 25/1988በኋላ ከመሆኑ አንፃር የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ክርክር የተለየ ባህርይ ከግምት ውስጥ በማስገባት ሕግ አውጭው ማናቸውም በክልሎች ውስጥ የሚነሳ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ የተከራካሪ ወገኖችን ማንነትን ከግምት ውስጥ ሳይገባ በክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት እንዲታይ መደነግጉን፤ አንድ ጉዳይ የተነሳው በክልል የመጀመሪያ ፍርድቤት ከሆነ ደግሞ ጉዳዩ በተነሳበት ክልል የሰበር ችሎት የተደራጀ እስከሆነ ድረስ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ሳይታይና ውሳኔው የመጨረሻ መሆኑ ሳይረጋገጥ በቀጥታ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ሊስተናገድ የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት አይኖርም* በማለት የቀረበውን አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል።

ከዚህ የፍርድ ቤቱ ውሳኔ መረዳት የምንችለው የሰበር መዝገብ ቁጥር 95298 የግል የስራ ክርክርን የተመለከተ ሲሆን በመዝገብ ቁጥር 94839ና መዝገብ ቁጥር 99426 ደግሞ የወል የስራ ክርክርን የተመለከቱ በመሆናቸው በሰበር መዝገብ ቁጥር 95298 የተሰጠው ውሳኔ በእነዚህ ሁለት መዝገቦች ለተያዘው ጉዳይ ምንም አይነት አግባብነት ያልነበረው መሆኑን ነው። ከዚህ አንፃር ሰበር ሰሚ ችሎቱ በቦርዶቹ የሚታዩ የወል የስራ ክርክሮችንና በክልል ፍርድቤቶች የሚታዩ የግለሰብ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳዮችን አንድ አድርጎ በመቁጠር በክልል የወረዳ ፍርድቤት ለተጀመረ የግል የአሠሪና ሠራተኛ ክርክር የሰጠውን ውሳኔ በአሠሪና ሠራተኛ ቦርድ በታየ የወል የስራ ክርክር ላይ መጥቀስና በዛ መዝገብ ላይ የሰጠውን ትንታኔና ምክንያት መሰረት አድርጎ ውሳኔ መስጠቱ ተገቢ አልነበረም።[48]

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰራው ሶስተኛው ስህተት ደግሞ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80(3)(ለ) የተቀመጠውን ሃሳብ በደንብ ያልመረመረ መሆኑ ነው። በሕገ መንግስቱ በግልጽ እንደተደነገገው የክልል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር ስልጣን የተሰጠው በክልል ጉዳዮች ብቻ እንጅ ለፌደራል ፍርድቤቶች በብቸኝነት በተሰጡ

[47] የሰበር መዝገብ ቁጥር 94102 በሰበር መዝገብ ቁጥር 94102 ቅጽ 16 እንደተጠቀሰው

[48] የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ በግርጌ ማስረታዎሻ ቁጥር እንደተገለጸው አንቀጽ 137-139140፣147፣ 153ና የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት በግርጌ ማስታዎሻ ቁጥር 2 እንደተገለጸው ፣ አንቀጽ 80

ጉዳዮች ጭምር እንዳልሆነ ግልጽ ነው፡፡ የክልል ጠቅላይ ፍርድቤት በውክልና ስልጣኑ በይግባኝ የሚመለከታቸውን ጉዳዮች የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት በይግባኝ የማየት ስልጣን አለው፡፡ አሁን የተያዘው ጉዳይ ደግሞ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጁ መሰረት በስረ ነገርና በይግባኝ የማየት ስልጣን የተሰጠው ለአሠሪና ሠራተኛ ቦርዱና ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት በመሆኑ የክልል ጠቅላይ ፍርድቤት በውክልና ስልጣኑ ተመልክቶ ውሳኔ የሰጠበትን የወል የስራ ክርክር የክልል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር የማየት ሕገ መንግስታዊ ስልጣን የለውም፡፡ ምክንያቱም የክልል ጠቅላይ ፍርድቤት የአሰሪና ሰራተኛ ቦርድ ውሳኔ የሰጠበትን የወል የስራ ክርክር ለማየት ስልጣን ያገኘው በአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ ሳይሆን በሕገ-መንግስቱ መሰረት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ስልጣን በውክልና የመመልከት ስልጣን ያለው በመሆኑ እንጅ ይህ ጉዳይ ለክልል ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ጉዳይ ስለሆነ አይደለም፡፡ ስለሆነም በነዚህ ሁለት መዝገቦች የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ችሎቱ በሕገ መንግስቱ የተሰጠውን ስልጣን አሳልፎ የሰጠ ከመሆኑም በላይ ሕጉን የተረጎመበት አግባብና የደረሰበት ድምዳሜ ምንም አይነት ህጋዊ ተቀባይነት የለውም፡፡

በመጨረሻም የሰበር ፍርድቤት የደረሰበትን ድምዳሜ ተቀባይነቱን ጥያቄ ውስጥ የሚጥለው ፍርድ ቤቱ የያዘው አቋም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤቶች በተቋቋሙባቸው ክልሎች ያለውን አንድምታ በምናይበት ጊዜ ነው፡፡ ከዚህ ላይ የሰበር ችሎቱ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤቶች በተቋቋሙባቸው ክልሎች የሚገኙ ጠቅላይ ፍርድቤቶች በአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ የሚወሰኑ የወል የስራ ክርክሮችን በይግባኝ የማየት ስልጣን የሌላቸው መሆኑንና የይግባኝ ስልጣን የሚኖራቸው በክልሎቹ የተቋቋሙት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤቶች መሆናቸውን ከግንዛቤ ውስጥ አላስገባም፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ለወደፊቱ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤቶች ሲቋቋሙ የአሠሪና ሠራተኛ ቦርዶች በስረ ነገር የወሰኗቸውን የወል የስራ ክርክሮች በእነዚህ ቦታዎች የሚገኙ የክልል ጠቅላይ ፍርድቤቶች ጉዳዮቹን በይግባኝ የማየት ስልጣን ሙሉ በሙሉ ቀሪ እንደሚሆን ግልጽ ነው፡፡ ምክንያቱም የክልል ፍርድቤቶች የፌደራል ጉዳዮችን በውክልና የሚያዩት በጊዜያዊነትና የፌደራል ፍርድቤቶች በክልሎቹ እስከሚቋቋሙ ድረስ እንደሆነ ከሕገ መንግስቱ መረዳት ይቻላል፡፡[49] ሆኖም ግን ከላይ በቀረቡት ሁለት የሰበር መዝገቦች ከተሰጠው ውሳኔ መገንዘብ እንደምንችለው በክልሎች የሚነሱ የወል የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳዮች ወሳኝ ቦርድ መታየት ያለባቸው ቢሆንም እነዚህ ውሳኔዎች በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ሳይቀርቡ ለፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት በቀጥታ መቅረብ እንደማይችሉ ነው፡፡ በዚህ ውሳኔ መሰረት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት በተቋቋመባቸው ክልሎች የአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ ውሳኔዎችን በይግባኝ ማየት የሚችለው የተቋቋመው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት ቢሆንም ጉዳዩን በቅድሚያ በሰበር የማየት ስልጣን ያለው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ነው፡፡ ይህ ደግሞ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጁና ከሕገ-መንግስቱ መንፈስና እሳቤ ውጭ የሆነ አረዳድ ነው፡፡ ምክንያቱም በፌደራል ፍርድቤቶች ታይተው የመጨረሻ ውሳኔ በተሰጠባቸው ጉዳዮች የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤትን ጉዳዮቹን በሰበር ለማየት የሚያስችል ምንም አይነት ሕገ-መንግስታዊ ስልጣን የላቸውም፡፡ በመሆኑም ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ይህንን ውሳኔ የወሰነው በተለያዩ ክልሎች የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤቶች ተቋቁመው ባሉበት ሁኔታና ይህ ውሳኔ በእነዚህ ፍርደ ቤቶች ላይ ሊያመጣው የሚችለውን አንድምታ ከግምት ውስጥ ሳያስገባ ነው፡፡

[49] የኢፌዲሪ ሕገ መንግስቱ በግርጌ ማስታዎሻ ቁጥር 2 እንደተገለጸው ፣ አንቀጽ 78 (2)

## ማጠቃለያ

ከሁለቱ መዝገቦች መረዳት የምንችለው ጉዳዮቹ ከክልል የአሰሪና ሰራተኛ ቦርድ የተጀመሩና ቦርዱ የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለክልሎቹ ጠቅላይ ፍርድቤት በይገባኝ ከቀረቡ በኋላ ፍርድ ቤቶቹ ጉዳዩን ተመልክተው የመጨረሻ ውሳኔ የሰጡት በሕገ መንግስቱ የተሰጣቸውን ውክልና መሰረት አድርገው በመሆኑ የሰበር አቤቱታ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቧል፡፡ የፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎትም ወደጉዳዩ ፍሬ ነገር ከመግባቱ በፊት ጉዳዮቹ ለሰበር ፍርድ ቤቱ ለመቅረብ የሚያስችል የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠባቸው ጉዳዮች ናቸው ወይ? የሚለውን በጭብጥነት በመያዝ ጉዳዩን መርምሮ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የሰበር ሰሚ ችሎቱም ይህ ጉዳይ በክልል ጠቅላይ ፍርድቤቶች የታየ በመሆኑ እና በየክልሎቹ ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሳይታዩ መምጣታቸው የመጨረሻ ውሳኔ ተሰጥቶባቸዋል ለማለት ስለማያስችል በአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ መሰረት ተደርገው የሚቀርቡ የስራ ክርክሮች በክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ያልታየ ውሳኔን ችሎቱ የሚያስተናግድበት አግባብ የለም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የሰበር ሰሚ ችሎቱ ጉዳዩን የተገነዘበበት፣ ጭብጥ የያዘበት ብሎም ጉዳዩን እና ህጎቹን የመረመረበት አግባበት ትክክለኛውን አካሄድ የተከተለ አልነበረም፡፡ በተለይም ጉዳዩ ከአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ የመነጨ መሆኑን ከመጥቀስ በስተቀር በአዋጁ መሰረት ቦርዱ ውሳኔ የሰጠበትንጉዳይ በይግባኝ የማየት ስልጣን በመሰረታዊነት የማን ነው? የክልሉ ጠቅላይ ፍርድቤት የአሰሪና ሰራተኛ ቦርድ የሚወስናቸውን የወል የስራ ክርክሮች በይግባኝ የመመልከት መብት ያገኘው በአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ መሰረት ነው ወይስ በሕገ-መንግስቱ በተሰጠው ውክልና? የክልል ጠቅላይ ፍርድቤት በውክልና ስልጣኑ ተመልክቶ የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠባቸውን ጉዳዮች በሰበር የመመልከት ስልጣን የማን ነው? የሚሉትን ጉዳዮች በጭብጥነት ይዞ አልመረመረም፡፡ በመሆኑን እነዚህን ጭብጦች ሳይመረምር ማንኛውም የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ የጉዳዩ መነሻ ምንም ይሁን ምን በክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ሳይታይ እና የመጨረሻ ውሳኔ ሳይሰጥበት ወደ ፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት መቅረብ የለበትም በማለት የደረሰበት ድምዳሜና የሰጠው ውሳኔ ትክክል ካለመሆኑም በላይ ሕገ-መንግስቱንና አግባብነት ያላቸውን ሕጎች ከግምት ውስጥ ያስገባ አይደለም፡፡

# Cassation Review Power over Collective Labor Dispute: Whose Jurisdiction is it; the Federal or Regional Supreme Courts? A Case Comment.

*Tegegne Zergaw*[*]

***Abstract***

Collective labor disputes normally fall under the original jurisdiction of the Federal Courts, to be specific the Federal High Court, and that regional courts have only delegated power. In its different decisions, the Federal Supreme Court cassation division ruled that it lacks jurisdiction to entertain collective labor disputes decided by the Regional Supreme Courts in their appellate jurisdiction unless the Cassation remedy at Regional Supreme Courts is also exhausted. After such decision of the Federal Supreme Court, it becomes the norm that any collective labor dispute that was finally decided by the Regional Supreme Courts, at appellate level and through delegated power, is not eligible to be entertained by the Federal Cassation division before it is finally settled by the Regional Supreme Courts cassation bench. Therefore, this case comment aims at examining whether or not this position of the Federal Supreme Court is in line with the Constitution and other relevant laws of the country. In order to achieve these objectives, two relevant decisions of the Federal Cassation bench and relevant laws of the country are examined thoroughly. The findings of the study revealed that the decision of the Federal Cassation division is not in line with the Constitution and other relevant laws of the country. Collective labor dispute falls under the exclusive jurisdiction of the federal courts, and the regional Supreme Court entertain such matters only through delegated power. Acccording to the constitutional arrangement on delegation of power, the Regional Supreme Courts lack delegated power to entertain Federal Matters through cassation.Hence, once the Regional Supreme Courts passed a final decision over collective labor dispute through appeal, it is only the the federal Supreme Court that is entitled to entertain the case through cassation.

***Keywords:*** Collective labor dispute, Appellate Jurisdiction, Cassation Jurisdiction, Delegated power, Federal Supreme Court, Regional supreme Courts.

[*] LL.B degree in Law (Jimma University), LL.M degree in Business and Corporate law (Bahir Dar University), Lecturer at Bahir Dar University school of law Email: tegegne.zergaw@gmail.com